- እግዚአብሔር ዮሴፍን የጠበቀው ለምንድን ነው?

- ዮሴፍ ኃጢአተኛ ሆኖ መወለዱን ያውቅ ስለነበር።

- ዮሴፍ ኃጢአቱ የዘላለም ሞት እንደሚያስከትልበት ያውቅ ስለነበር።

- ዮሴፍ እግዚአብሔር ብቻ ሊያድነው እንደሚችል ያውቅ ስለነበር።

- ዮሴፍ እግዚአብሔር የሚያድነውን አዳኝ እንደሚልክለት ያምን ስለነበር።

- ዮሴፍ በእሥር ቤት ሆኖ ሳለ እግዚአብሔር የረሳው ይመስልሃል?

- አልረሳውም።

- በሚቀጥለው ትምህርት እግዚአብሔር ለዮሴፍ ምን እንዳደረገለት እናነብባለን።



## ትምህርት 24

1. አብርሃም ሚስቱ ሣራ ከሞተች በኋላ ልጁ ይስሐቅ እንዲጋባ ምን አደረገለት?

ሀ- አብርሃም ለልጁ ለይስሐቅ ሚስት አጋባው።

2. የይስሐቅ ሚስት ስሟ ማን ነበረ?

ሀ- ርብቃ።

3. የርብቃ ልጆች ከመወለዳቸው በፊት፥ እግዚአብሔር ስለእነርሱ ሁሉንም ነገር እንዴት ሊያወቅ ቻለ?

ሀ- እግዚአብሔር ስለ ሁሉም ሰው ሁሉንም ነገር ያውቃል።

ለ- ከእግዚአብሔር የተሰወረ አንድም ነገር የለም።

4. ርብቃ የወለደቻቸው የሁለት መንታ ወንዶች ልጆች ስም ማን ማን ይባል ነበር?

ሀ- ዔሳውና ያዕቆብ።

5. ዔሳው በእግዚአብሔር ያምን ነበር?

ሀ- አያምንም።

6. ያዕቆብ በእግዚአብሔር ያምን ነበር?

ሀ- አዎን።

7. እግዚአብሔር ከያዕቆብ የዘር ግንድ አዳኝ ለመላክ የፈለገው ለምንድን ነው?

ሀ- ዔሳው በእግዚአብሔር ስላላመነ ነው።

8. እግዚአብሔር በሕልም ለያዕቆብ ምን አሳየው?

ሀ- ለያዕቆብ መሰላል አሳየው።

9. የመሰላሉ የታችኛው ጫፍ የት ደርሶ ነበር?

ሀ- የመሰላሉ የታችኛው ጫፍ መሬትን ነክቶ ነበር።

10. የመሰላሉ የላይኛው ጫፍ የት ደርሶ ነበር?

ሀ- የመሰላሉ የላይኛው ጫፍ ሰማይን ነክቶ ነበር።

11. መሰላሉ መሬትን መንካቱና እስከ ሰማይ መድረሱ ምንን ያሳያል?

ሀ- መሰላሉ መሬትንና ሰማይን በአንድነት ያገናኘ መሆኑን።

12. እግዚአብሔር ለያዕቆብ ይህንን ሕልም ለምን አሳየው?

ሀ- በዚህ ህልም እግዚአብሔር ያዕቆብን ስለሚመጣው አዳኝ እያስተማረው ነበር።

13. እግዚአብሔር በሕልም ስለ አዳኙ ለያዕቆብ ምን እያስተማረው ነበር?

ሀ- ልክ መሰላሉ ሰማይንና ምድርን እንዳገናኘ ሁሉ እግዚአብሔር የሚልከው አዳኝ በምድር የሚኖሩትን ሰዎችንና በሰማይ የሚኖረውን እግዚአብሔርን እንደሚያገናኛቸው።

14. እግዚአብሔር አዳኝ እንደሚልክ የሰጠውን ተስፋ የማይረሳው ለምንድን ነው?

ሀ- እግዚአብሔር የማይረሳ ስለሆነ።

ለ- እግዚአብሔር ስለማይለወጥ።

ሐ- እግዚአብሔር ሁልጊዜ ተስፋውን ስለሚጠብቅ።

15. ያዕቆብ ለብዙ ዓመታት በካራን ከኖረ በኋላ እግዚአብሔር ምን እንዲያደርግ ነገረው?

ሀ- ያዕቆብ ካራንን ለቅቆ ወደ ከነዓን ምድር እንዲመለስ ነገረው።



- እግዚአብሔር በእርሱ የሚያምነውን ሰው ፈጽሞ አይተውም።

- እግዚአብሔር ሁሉ ጊዜ ከዮሴፍ ጋር ነበረ።

- በእስር ቤት ሳለ እንኳ እግዚአብሔር ከዮሴፍ ጋር ነበረ።

ዘፍጥረት 39-20ለ-23

20- ይሁን እንጂ ዮሴፍ እዚያ እስር ቤት ባለበት ጊዜ ሁሉ፣

21- እግዚአብሔ ከእርሱ ጋር ነበር፤ ቸርነቱንም አበዛለት፣ በወኅኒ አዛዡም ዘንድ ሞገስን ሰጠው።

22- ስለዚህ የወኅኒው አዛዥ ዮሴፍን የእስረኞች ሁሉ አለቃ አደረገው፤ በእስር ቤቱ ስላለው ነገር ሁሉ ኃላፊ ሆነ።

23- እግዚአብሔር ከዮሴፍ ጋር ሆኖ ሥራውን ሁሉ ያሳካለት ስለነበር የወኅኒ ቤት አዛዡ በዮሴፍ ኃላፊነት ሥር ስላለው ስለ ማንኛውም ጉዳይ ሐሳብ አይገባውም ነበር።

- ወንድሞቹ ቢጠሉትም ዮሴፍ በእግዚአብሔር ማመኑን ቀጠለ።

- ወንድሞቹ እንደ ባሪያ ቢሸጡትም ዮሴፍ በእግዚአብሔር ማመኑን ቀጠለ።

- የጲጥፋራ ሚስት በሐሰት ብትወነጅለውም ዮሴፍ በእግዚአብሔር ማመኑን ቀጠለ።

- እሥር ቤት ቢጣልም ዮሴፍ በእግዚአብሔር ማመኑን ቀጠለ።

- ዮሴፍን በእሥር ቤት ሳለ የጠበቀው ማን ነበረ?

- እግዚአብሔር።

15- ለእርዳታ መጮኼን ሲሰማም፣ ልብሱን ከአጠገቤ ጥሎት ሸሽቶ ከቤት ወጣ።»

- ዮሴፍ በእግዚአብሔር ሰለሚያምን ከጲጥፋራ ሚስት ጋር አልተኛም አለ።

- ዮሴፍ አብሯት ለመተኛት ስላልፈቀደ የጲጥፋራ ሚስት ዮሴፍን በሐሰት ከሰሰችው።

- ጲጥፋራ ወደ ቤት ሲመለስ ምን ተፈጸመ?

ዘፍጥረት 39፡16-20ሀ

16- ጌታውም ወደ ቤት እስኪመለስ ድረስ ልብሱን አጠገቧ አቆየችው።
17- ታሪኩን እንዲህ ስትል ነገረችው፡ «አንተ ያመጣኸው ዕብራዊ ባሪያ መሣለቂያ ሊያደርገኝ ወዳለሁበት ሰተት ብሎ ገባ፤
18- ታዲያ እኔ ድረሱልኝ ብዬ ስጮኽ፣ ልብሱን አጠገበ ጥሎ ሸሽቶ ወጣ።»
19- ጌታውም «ባሪያህ እንዲህ አደረገኝ» ብላ ሚስቱ የነገረችውን ታሪክ ሲሰማ ተቆጣ።
20- ጌታውም ዮሴፍን ወስዶ የንጉሥ እስረኞች ወደ ተጋዙበት እስር ቤት አስገባው።

- ጲጥፋራ ወደ ቤት እንደ መጣ የሚስቱን ውሸት አምኖ ዮሴፍን እስር ቤት አስገባው።

- ዮሴፍ በእስር ቤት በነበረ ጊዜ እግዚአብሔር ተወውን?

- አልተወውም።



- ያዕቆብን ከክፉ ሁሉ ጠብቆ ከካራን ወደ ከነዓን ምድር ያመጣው ማን ነው?

- እግዚአብሔር።

ዘፍጥረት 37፡1

1- ያዕቆብ አባቱ በኖረበት በከነዓን ምድር ተቀመጠ።

- እግዚአብሔር ለያዕቆብ የሰጠው አዲስ ስም ማን ነበር?

- እስራኤል።

ዘፍጥረት 37፡3

3- እስራኤል ዮሴፍን በስተርጅናው ስለ ወለደው፣ ከልጆቹ ሁሉ አብልጦ ይወደው ነበር። በኅብረ ቀለማት ያጌጠ እጀ ጠባብም አደረገለት።

- ያዕቆብ ስንት ወንዶች ልጆች ነበሩት?

- ዐሥራ ሁለት።

- ያዕቆብ ዐሥራ ሁለት ልጆች ነበሩት ነገር ግን ከልጆቹ ሁሉ አንደኛውን የበለጠ ይወደው ነበር።

- ያዕቆብ ከልጆቹ ሁሉ የበለጠ የሚወደው ልጅ ስሙ ማን ነበር?

- ዮሴፍ።

- ያዕቆብ ዮሴፍን ከልጆቹ ሁሉ ይልቅ ስለ ወደደው ጌጠኛ ልብስ አለበሰው።

- ያዕቆብ ዮሴፍን ከልጆች ሁሉ አብልጦ ስለ ወደደው ወንድሞቹ በዮሴፍ ላይ ምን አሰቡ?

- በቅናት ተነሡበት ጠሉትም።

- የዮሴፍ ወንድሞች ዮሴፍን የጠሉበት ሌላው ምክንያት ዮሴፍ የወንድሞቹን ጥፋት ለያዕቆብ ይነግር ስለ ነበር ነው።

ዘፍጥረት 37፡2 & 4

2- ዮሴፍ የአሥራ ሰባት ዓመት ወጣት በነበረ ጊዜ፣ ከአባቱ ሚስቶች ከባላና ከዘለፋ ከተወለዱት ወንድሞቹ ጋር የአባቱን በጐችና ፍየሎች ይጠብቅ ነበር። እርሱም ስለ ወንድሞቹ ድርጊት ለአባቱ መጥፎ ወሬ ይዞለት መጣ።

4- ወንድሞቹም፣ አባታቸው ከእነርሱ አብልጦ የሚወደው መሆኑን ሲያዩ፣ ዮሴፍን ጠሉት፤ በቅን አንደበትም ሊያናግሩት አልቻሉም።

- ሰዎች በሌሎች ሰዎች ላይ የሚቆጡት ለምንድን ነው?

- ሰዎች ሌሎችን ሰዎች የሚጠሉት ለምንድን ነው?

- ምክንያቱም እያንዳንዱ ሰው የሚወለደው ከእግዚአብሔር ተለይቶ ስለሆን ነው።

- ምክንያቱም እያንዳንዱ ሰው ኃጢአት በልቡ ይዞ ስለሚወለድ ነው።

- ምክንያቱም እያንዳንዱ ሰው የሰይጣን ልጅ ሆኖ ስለሚወለድ ነው።



- የዮሴፍ ወንድሞች ዮሴፍን እንደ ባሪያ ቢሸጡትም እግዚአብሔር ዮሴፍን አልተወውም።

- ዮሴፍ በእግዚአብሔር ስላመነ እግዚአብሔር ዮሴፍን ባረከው።

- አንድ ቀን ጲጥፋራ ወደ ሥራው ሄዶ ሳለ በዮሴፍ አንድ ነገር ደረሰበት።

ዘፍጥረት 39፡6ለ-15

6- ዮሴፍ ጥሩ ቁመና ያለውና መልከ መልካም ነበር።

7- እያደርም የጌታው ሚስት ዓይኗን ጣለችበት፤ አፍ አውጥታም፣ «አብረኸኝ ተኛ» አለችው።

8- እርሱ ግን ፈቃደኛ አልሆነም፤ እንዲህም አላት፤ «ጌታዬ ያለውን ሁሉ በኃላፊነት ስለ ሰጠኝ፣ በቤቱ ውስጥ ስላለው ሁሉ ምንም የሚያውቀው ነገር የለም።

9- በዚህ ቤት ላይ ከእኔ የበለጠ ኃላፊነት ያለው ማንም የለም፤ እርሱ ያልሰጠኝ ነገር ቢኖር፣ አንቺን ብቻ ነው፤ ያውም ሚስቱ ስለ ሆንሽ ነው፤ ታዲያ እኔ ይህን ክፉ ድርጊት ፈጽሜ እንዴት በእግዚአብሔር ፊት ኃጢአት እሠራለሁ?»

10- ምንም እንኳ ዮሴፍን በየቀኑ ብትጐተጕተውም፣ አልሰማትም፤ ከእርሷ ጋር መተኛት ይቅርና አብሯትም መሆን አልፈቀደም።

11- አንድ ቀን ዮሴፍ የዕለት ተግባሩን ለማከናወን ወደ ቤት ገባ። ከቤቱ አገልጋዮችም አንድም ሰው በቤት ውስጥ አልነበረም።

12- እርሷም ልብሱን ጨምድዳ ይዛ «በል አብረኸኝ ተኛ» አለችው። እርሱ ግን ልብሱን እጇ ላይ ጥሎ ሸሽቶ ከቤት ወጣ።

13- እርሷም ልብሱን እጇ ላይ ጥሎ ሸሽቶ መውጣቱን ባየች ጊዜ፣

14- የቤት አገልጋዮቿን ጠራች፤ እንዲህም አለቻቸው፤ «እያችሁ፤ ለካስ ይህ ዕብራዊ የመጣው መሣለቂያ ሊያደርገን ኖሮአል! እዚህ ድረስ ሰተት ብሎ ገብቶ ካልተኛሁሽ አለኝ፤ እኔም ጩኼቱን ለቀቅሁት

- ለጲጥፋራ።
- እግዚአብሔር ዮሴፍን ትቶት ነበር?

- አልተወውም።

- እግዚአብሔር በእርሱ የሚያምነውን ሰው ፈጽሞ አይተወውም።

- እግዚአብሔር ሁል ጊዜ ከዮሴፍ ጋር ነበር።

- ዮሴፍ ወደ ጲጥፋራ ከመጣ በኋላ ምን እንደ ደረሰበት እናንብብ፡

ዘፍጥረት 39፥2-6ሀ

2- እግዚአብሔር ከዮሴፍ ጋር ነበር። ኑሮው ተቃናለት፤ እርሱም በግብፃዊው አሳዳሪው ቤት ኖረ።

3- አሳዳሪውም እግዚአብሔር ከእርሱ ጋር እንዳለና ሥራውም ሁሉ እንዲከናወንለት ባየ ጊዜ

4- ዮሴፍ በእርሱ ዘንድ ሞገስ አገኘ፤ የቅርብ አገልጋዩም ሆነ። ጲጥፋራ በቤቱ ላይ ሾመው። ያለውንም ሀብት ሁሉ በኃላፊነት ሰጠው።

5- ዮሴፍ በጲጥፋራ ቤትና ባለው ሀብት ሁሉ ላይ ከተሾመበት ጊዜ ጀምሮ እግዚአብሔር የግብፃዊውን ቤት ባረከ፤ የእግዚአብሔርም በረከት በግቢም በውጭም ባለው የጲጥፋራ ሀብት ንብረት ሁሉ ላይ ሆነ።

6- ስለዚህ ጲጥፋራ ባለው ሁሉ ላይ ሥልጣን ሰጠው፤ የቀረበለትንም ከመመገብ በስተቀር ማናቸውንም ጉዳይ በዮሴፍ ላይ ጥሎ ነበር።

- የዮሴፍ ወንድሞች ዮሴፍን ቢጠሉትም እግዚአብሔር ግን ዮሴፍን አልተወውም።



- የዮሴፍ ወንድሞች ዮሴፍን የጠሉት፥ ከእግዚአብሔር የተለዩ ሆነው ስለተወለዱ ነው።

- የዮሴፍ ወንድሞች ዮሴፍን የጠሉት፥ ኃጢአት በልባቸው ይዘው ስለተወለዱ ነው።

- የዮሴፍ ወንድሞች ዮሴፍን የጠሉት፥ የሰይጣን ልጆች ሆነው ስለ ተወለዱ ነው።

- እያንዳንዱ ሰው የተወለደው ከእግዚአብሔር ተለይቶ ነው፤ ስለዚህ እኛ ራሳችንን መለወጥ አንችልም።

- እያንዳንዱ ሰው የተወለደው ኃጢአት በልቡ ይዞ ነው፤ ስለዚህ እኛ ራሳችንን መለወጥ አንችልም።

- እያንዳንዱ ሰው የተወለደው የሰይጣን ልጅ ሆኖ ነው፤ ስለዚህ እኛ ራሳችንን መለወጥ አንችልም።

- አንድ ቀን እግዚአብሔር ለዮሴፍ ሕልም አሳየው።

ዘፍጥረት 37፥5-8

5- ዮሴፍም ሕልም አለመ። ሕልሙንም ለወንድሞቹ ሲነግራቸው የባሰ ጠሉት።

6- እርሱም እንዲህ አላቸው፤ «ያየሁትን ሕልም ልንገራችሁ፤ አድምጡኝ፤

7- እኛ ሁላችን በእርሻ ውስጥ ነዶ እናስር ነበር፤ የእኔ ነዶ በድንገት ተነሥታ ቀጥ ብላ ቆመች፤ የእናንተም ነዶዎች ዙሪያዋን ከበው ለእኔ ነዶ ሰገዱላት። »

8- ወንድሞቹም «ለካስ በላያችን ለመንገሥ ታስባለህና! ለመሆኑ አንተ እኛን ልትገዛ!» አሉት። ስለ ሕልሙና ስለተናገረው ቃል ከፊት ይልቅ ጠሉት።

- እግዚአብሔር ለዮሴፍ ያሳየው የመጀመርያው ሕልም ምን ነበር?

- በሕልም ዮሴፍና ወንድሞቹ በማሳ ላይ እህል አጭደው ነዶ ያስሩ ነበር።

- ከዚያም የወንድሞቹ ነዶዎች ለዮሴፍ ነዶ ሰገዱ።

- እግዚአብሔር ካሳየው ሕልም የተነሣ የዮሴፍ ወንድሞች ዮሴፍን የበለጠ ጠሉት።

- ከጥቂት ጊዜ በኋላ እግዚአብሔር ለዮሴፍ ሁለተኛ ሕልም አሳየው።

ዘፍጥረት 37፥9-11

9- እንደገናም ሌላ ሕልም አለመ፤ ለወንድሞቹም፣ «እነሆ፤ ሌላ ሕልም አለምሁ፤ ፀሐይና ጨረቃ፣ አሥራ አንድ ከዋክብትም ሲሰግዱልኝ አየሁ» ብሎ ነገራቸው።

10- ሕልሙን ለአባቱና ለወንድሞቹ በነገራቸው ጊዜ፣ አባቱ፣ «ይህ ያየኸው ሕልም ምንድን ነው? እኔና እናትህ ወንድሞችህም በፊትህ ወደ ምድር ተጐንብሰን በእርግጥ ልንሰግድልህ ነው?» ሲል ገሠጸው።

11- ወንድሞቹ ቀኑበት፣ አባቱ ግን ነገሩን በልቡ ያዘው።

- እግዚአብሔር ለዮሴፍ ያሳየው ሁለተኛ ሕልም ምን ነበር?

- በሕልሙ ፀሐይ ጨረቃና ከዋክብት ያይ ነበር።



- የዮሴፍ ወንድሞች ዮሴፍን እንደ ባሪያ ሸጡት።

- ከዚያ ወንድሞቹ አባታቸውን አታለሉት።

- ያዕቆብም ዮሴፍ እንደ ሞተ አሰበ።

- የዮሴፍ ወንድሞች ዮሴፍን ጠሉት።

- የዮሴፍ ወንድሞች ጥላቻ ዮሴፍን እንደ ባሪያ ወደ መሸጥ አደረሳቸው።

- የዮሴፍ ወንድሞች ጥላቻ አባታቸውን ወደ ማታለል መራቸው።

- ጥላቻ ሁልጊዜ ወደ ባሰ ኃጢአት ይመራል።

- ዮሴፍ ሞቶ ነበር?
- አልሞተም።

- ዮሴፍ የት ነበር?
- ዮሴፍ በግብጽ ነበር።

ዘፍጥረት 39፥1

1- በዚህ ጊዜ ዮሴፍ ወደ ግብፅ ተወስዶ ነበር፤ ከፈርዖን ሹማምንት አንዱ የሆነውም የዘበኞች አለቃ፣ ግብፃዊው ጲጥፋራ ወደዚያ ከወሰዱት ከእስማኤላውያን ነጋዴዎች እጅ ገዛው።

- የባሪያ ነጋዴዎቹ ዮሴፍን የሸጡት ለማን ነበር?

- ሮቤል ከሄደበት ሲመለስ የዮሴፍ ወንድሞች ምን አደረጉ?

ዘፍጥረት 37፡29-31

29- ሮቤል ወደ ጉድጓዱ ተመልሶ ሲያይ፣ ዮሴፍን በማጣቱ ልብሱን በኀዘን ቀደደ።

30- ወደ ወንድሞቹም ተመልሶ፣ «ብላቴናው ጉድጓድ ውስጥ የለም፤ የት አባቴ ልሂድ?» አለ።

31- ከዚያም የዮሴፍን እጀ ጠባብ ወሰዱ፤ አንድ ፍየልም አርደው እጀ ጠባቡን በደሙ ነከሩት።

- የዮሴፍ ወንድሞች የዮሴፍን ልብስ ወስደው፥ ፍየል አርደው በደም ነከሩት።

- ከዚያም የዮሴፍ ወንድሞች በፍየል ደም የተነከረውን የዮሴፍን ልብስ ወስደው ለአባታቸው ሰጡት።

ዘፍጥረት 37፡32-35

32- በኅብረ ቀለማት ያጌጠችውን እጀ ጠባብ ወደ አባታቸው ወስደው፣ «ይህን ወድቆ አገኘነው፤ የልጅህ እጀ ጠባብ መሆን አለመሆኑን እስቲ እየው?» አሉት።

33- እርሱም ልብሱን አውቆት፣ «ይህማ የልጄ እጀ ጠባብ ነው!፤ ክፉ አውሬ በልቶታል፣ በእርግጥም ዮሴፍ ተቦጫጭቆአል» አለ።

34- ከዚህ በኋላ ያዕቆብ ልብሱን ቀደደ፤ ማቅም ለብሶ ስለ ልጁ ብዙ ቀን አለቀሰ፤

35- ወንዶችና ሴቶች ልጆቹም ሁሉ ሊያጽናኑት መጡ፤ እርሱ ግን ሊጽናና ባለመቻሉ «በኀዘን እየተኰራመትሁ ልጄ ወዳለበት መቃብር እወርዳለሁ» አለ። ስለ ልጁም አለቀሰ።



- ከዚያም ፀሐይ ጨረቃና አሥራ አንዱ ክዋክብት ለዮሴፍ ሰገዱለት።

- በሕልሙ ፀሐይ የሚያመለክተው ማንን ነው?
- የዮሴፍን አባት።

- በሕልሙ ጨረቃ የሚያመለክተው ማንን ነው?
- የዮሴፍን እናት።

- በሕልሙ አሥራ አንድ ክዋክብት የሚያመለክቱት እነማንን ነበር?
- የዮሴፍን አሥራ አንድ ወንድሞች¾Ã¾Ã¾ÃN።

- የሁለቱም ሕልሞች ትርጉም ምን ነበር?

- አንድ ቀን እግዚአብሔር ዮሴፍን አለቃ እንደሚያደርገውና የዮሴፍ ቤተሰብ በሙሉ ለእርሱ እንደሚሰግዱለት።

- የዮሴፍን የወደፊት ሁኔታ የሚያውቀውና ሊሆን ያለውን በሕልም ያሳየው ማን ነበር?

- እግዚአብሔር።

- እግዚአብሔር የዮሴፍን የወደፊት ሁኔታ እንደሚያውቅ ሁሉ የእኛንም የወደፊት ሁኔታ ያውቃል።

- ወደፊት ከሚገጥሙን ሁኔታዎች እግዚአብሔር የሚያውቀው ስንቱን ነው?

- እግዚአብሔር ሁሉንም የወደፊት ሁኔታችንን ያውቃል።

- እግዚአብሔር ለዮሴፍ ካሳየው ሕልም የተነሣ የዮሴፍ ወንድሞች ዮሴፍን ከበፊቱ የበለጠ ጠሉት።

- አንድ ቀን ዮሴፍ በሜዳ ከብት የሚጠብቁትን ወንድሞቹን ሊጐበኝ ሄደ።

ዘፍጥረት 37፥17ለ-20

17- ከዚያም ዮሴፍ ወንድሞቹን ፍለጋ ሄደ፤ ዶታይን አቅራቢያም አገኛቸው።

18- ወንድሞቹም ዮሴፍ ወደ እነርሱ ሲመጣ በሩቅ አዩት፤ ወደ ነበሩበትም ስፍራ ከመድረሱ በፊት ሊገድሉት ተማከሩ።

19- እነርሱም እንዲህ ተባባሉ፤ «ያ ሕልም አላሚ መጣ፤

20- ኑ እንግደለውና ከጉድጓዶቹ በአንዱ ውስጥ እንጣለው፤ ከዚያም ክፉ አውሬ ነጥቆ በላው! እንላለን፤ እስቲ ሕልሞቹ ሲፈጸሙ እናያለን።»

- የዮሴፍ ወንድሞች እጅግ በጣም ስለ ጠሉት ሊገድሉት ፈለጉ።

- ነገር ግን የያዕቆብ የበኩር ልጅ ሮቤል ዮሴፍን ለመዳን ወሰነ።

ዘፍጥረት 37፥21-24

21- ሮቤል ግን ይህን ምክር ሲሰማ ከእጃቸው ሊያድነው ፈለገ። እንዲህም አለ፤ «ሕይወቱ በእጃችን አትለፍ።

22- የሰው ደም አታፍስሱ፤ እዚህ ምድረ በዳ ጉድጓድ ውስጥ ጣሉት እንጂ እጃችሁን አታንሡበት።» ሮቤል ይህን ያለው ሕይወቱን ከእጃቸው አትርፎ ወደ አባቱ ሊመልሰው አስቦ ነበር።

23- ዮሴፍ ወደ ወንድሞቹ እንደ ደረሰ፤ የለበሳትን በኅብረ ቀለማት ያጌጠች እጀ ጠባቡን ገፈፉት፤



24- ይዘውም ወደ ጉድጓድ ጣሉት፤ ጉድጓዱም ውኃ የሌለበት ደረቅ ነበር።

- የዮሴፍ ወንድሞች በዮሴፍ ላይ ምን አደረጉበት?

- ልብሱን ገፍፈው ወደ ደረቅ ጉድጓድ ጣሉት።

- ሮቤል ከሄደ በኋላ የዮሴፍ ወንድሞች በዮሴፍ ላይ ምን አደረጉበት?

ዘፍጥረት 37፥25-28

25- ምግባቸውን ለመብላት ተቀመጡ፤ አሻግረው ሲመለከቱም ከገለዓድ የሚመጡ የእስማኤላውያን ነጋዴዎችን የግመል ኳዝ አዩ። ነጋዴዎቹ ሽቶ፣ በለስና ከርቤ በግመሎቻቸው ጭነው ወደ ግብፅ የሚወርዱ ነበሩ።

26- ይሁዳም ወንድሞቹን እንዲህ አላቸው፤ «ወንድማችንን መግደልና አማሟቱን መደበቅ ምን ይጠቅመናል?

27- ከዚህ ይልቅ ለእስማኤላውያን ነጋዴዎች እንሽጠው፤ እጃችንን ግን በእርሱ ላይ እናንሣ። ምንም ቢሆን እኮ ወንድማችን፤ ሥጋችን ነው።»

28- ወንድሞቹም በአሳቡ ተስማሙ። የምድያም ነጋዴዎችም እነርሱ ዘንድ እንደ ደረሱ፤ ወንድሞቹ ዮሴፍን ከጉድጓድ አውጥተው ለእስማኤላውያን በሃያ ጥሬ ብር ሸጡላቸው፤ እነርሱም ዮሴፍን ወደ ግብፅ ወሰዱት።»

- የዮሴፍ ወንድሞች ዮሴፍን እንደ ባሪያ ለባሪያ ነጋዴዎች ሸጡት።

- ባሪያ ነጋዴዎች ዮሴፍን ወዴት ወሰዱት?

- ወደ ግብፅ።